# በትራንስፖርት ሚኒስቴር የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ

# የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 657/2013

መስከረም 2006 ዓ.ም

# ማውጫ


መግቢያ ........................................................ 4

ክፍል አንድ፡ - ጠቅላላ ........................................................ 4

1. አጭር ርዕስ ........................................................ 4

2. ትርጓሜ ........................................................ 4

3. የመመሪያው ዓላማ ........................................................ 5

4. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን ........................................................ 5

**ክፍል ሁለት፡ - አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም ........................................................ 5**

**ንዑስ ክፍል አንድ አስቸኳይ ህክምና ........................................................ 6**

5. የተሽከርካሪ አደጋ ........................................................ **Error! Bookmark not defined.**

6. የተሽከረካሪ **አደጋን ለመድን ሰጭ ስለማሳወቅ** ........................................................ 6

**7.**መድን የሌላቸዉና ያልታወቁ ተሽከረካሪዎች ........................................................ 9

ክፍል ሶስት፡ - የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር ........................................................ 13

**8. የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ........................................................ 13**

**9. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ምንጭና የሚከፉ ስሌት ........................................................ 13**

**10. የተዘዋዋሪ ፈንድ የመዋጮ/ድርሻ ክፍያ ........................................................ 14**

**11. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ሥርጭት ........................................................ 14**

**12. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ተመንና ድርሻ በዓመቱ ከሚቀርበው የአገልግሎት ክፍያ ሲያንስና ሲበልጥ Error! Bookmark not defined.**

**13. የተዘዋዋሪ ፈንዱ የሂሳብ ዘመንና ኦዲት ስለማከደረግ ........................................................ 16**

**ክፍል አራት፡ - የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ ........................................................ 16**

**14. የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አደረጃጀትና ኃላፊነት ........................................................ 16**

ክፍል አምስት፡ - የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ........................................................ 18

**15. የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ........................................................ 18**

**16. የመድን ሰጪ ኩባንያዎች ........................................................ 18**

**17. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ........................................................ 18**

**18. የጤና ቢሮ (ጽ/ቤት) ........................................................ 19**

**19. የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ........................................................ 19**

**20. የሕክምና ተቋማት ........................................................ 20**

**21. የፖሊስ /የትራፊክ ፖሊስ ........................................................ 20**

**22. ሌሎች አካላት** ........ 20

ክፍል ስድስት፡ – የተለያዩ ጉዳዮች ........ 20

**23. ቅሬታ አቀራረብ** ........ 20

**24. የተጭበረበሩ ሰነዶችና የሀሰት የክፍያ ጥያቄዎች** ........ 21

**25. ተፈፃሚ ት ስለሚኖራቸው /ስለሚይኖራቸው መሚያዎች፣ ደንቦች፣ ሕጎች ወይም አዋጆች** ........ 21

**26. መሚያወጣ ስለማሻሻል** ........ 21

**27. መሚያው የሚፀናበት ጊዜ /ዘመኑ** ........ 21

**28. አባሪዎች** ........

ሀ. የ2004 ዓ.ም የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመንና የመዋጮ ድርሻ ........ 22

ለ. የትራፊክ ፖሊስ የአሰቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማጠየቂያ ቅጽ ........ 22

ሐ. የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ........

መ. የሕክምና ተቋማት የአሰቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ ማጠየቂያ ቅጽ ........

ሠ. የሩብ ዓመት የአሰቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም ሪፖርት ........

ረ. የኤጀንሲው የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የአደጋ ማነወቂያ ቅጽ ........

ሰ. የአሰቸኳይ ህክምና አገልግሎት ብሮሽር (በሕክምና ተቋማት ድንገተኛ ክፍል የሚለጠፍ) ........

ሸ. የመድን ሰጪዎችና የኤጀንሲው የተመዘገበ አድራሻና ሌሎች መረጃዎች ........

## መግቢያ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን እና በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ለሚድረግና የህክምና ተቋማት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በወቅቱ ማግኘታቸውን ለሚረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ አሠራር ለማዘርጋትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ኃላፊነትን ግልጽ በሆነ መንገድ ማስቀመጥ አስፈላጊ በማሆኑ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ፡ - ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በትራንስፖርት ሚኒስቴር የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 657/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 የተሰጣቸው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ

1) **"ባለስልጣን"** ወይም **"ቢሮ"** ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ወይም የክልልና የከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ነው፡፡
2) **"የህክምና ተቋም"** ማለት ማንኛውም ከኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ወይም ከክልልና ከከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ህጋዊ ፈቃድ በማግኘት የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ የግል፣ ወይም የመንግስት የህክምና ተቋም ነው፡፡
3) **"አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 799 /2005 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 16 መሠረት በመንገድ ላይ በደረሰ በተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ ግለሰብ ከአደጋው ቦታ ወደ ህክምና ተቋም በሚጓጓዝበት ወቅት እና በህክምና ተቋሙ ድንገተኛ ክፍል ወስጥ የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት ነው፡፡

4) **"ተዘዋዋሪ ፈንድ"** ወይም **"ተዘዋዋሪ ገንዘብ"** ማለት የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀምን በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመድን ሰጪ ከባንያዎች በሚሰበሰቡ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ነጻ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ባለንብረቶች ወይም አስተዳዳሪዎችና ከኤጀንሲው በሚገኝ መዋጮ የሚቋቋምና በየጊዜው የሚታካ / የሚዋረረድ የገንዘብ ምንጭ ነው፡፡

5) **"ተጎጂ"** ማለት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው ነው፡፡

6) **"ያልተገለፁ "** በወንድ ፆታ የተገለጹት በሙሉ ለሴ ፆታ ያገለግላሉ፡፡

### 3. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት በህክምና ተቋማት ማግኘቱን ለማረጋገጥ፣ አገልግሎት የሰጠው የህክምና ተቋም ተገቢና ወቅታዊ ክፍያ እንዲያገኝ ለማድረግና፣ የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት በማሳወቅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚት ያለው ግልጽ የሆነ አንድ ወጥ አሠራር ለማስቀመጥ ነው፡፡

### 4. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ማንኛውም ሰው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት በማንኛውም የህክምና ተቋም፣ በፖሊስ፣ በትራፊክ ፖሊስ፣ በመድን ሰጪ ከባንያ፣ በኤጀንሲው፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በጤና ቢሮዎች፣ እንዲሁም በተሽከርካሪ ባለንብረት፣ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ተጎጂ ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት እና ክፍያ የመጠየቅ መብት ባለው ማንኛውም አካል ወይም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም

# ንዑስ ክፍል አንድ - አስቸኳይ ህክምና

### 5. የተሽከርካሪ አደጋ

የተሽከርካሪ አደጋ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ሥራ የሚጀምረው በተሽከርካሪ አደጋ መከሰት ምክንያት ሲሆን በንብረት ብቻ ላይ ከደረሰ ጉዳት በስተቀር ሌሎች በሰው ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች አገልግሎቱ ለማንኛውም ተጎጂ በህክምና ተቋማት እንዲሰጥ ምክንያት ይሆናል፡፡

### 6. የተሽከርካሪ አደጋን ለመድን ሰጪ ስለማሳወቅ

1. በዚህ በአንቀፅ 5 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 ማስረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር መድን ገቢው መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ ሚደረሱን ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ በ10 ቀን ውስጥ ለመድን ሰጭው ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የአደጋ ማሳወቂያው መንገድ በእያንዳንዱ የመድን ሰጪ ኩባንያ ጥቅም ላይ እንዲውል በተፈቀደ ማንኛውም ዘዴ ወይም የአደጋ ማሳወቂያ ቅጽ ለሚመለከተው የመድን ሰጪ ኩባንያ በተመዘገበ አድራሻ ሊሆን ይችላል፡፡
3. ኤጀንሲው ከመድን ሰጭዎች ጋር በጋራ በማስራት የኩባንያዎችን ስምና የተመዘገበ አድራሻ እንዲሁም ሌላ ለግንኙነት የሚያስፈልግ መረጃ በማዘጋጀት በየወቅቱ ሕብረተሰቡ እንዲያወቀው ያሰራጫል፡፡

## 7. መድን የሌላቸውና ያልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋን ለኤጀንሲው ስለማሳወቅ

1. መድን በሌላቸው ወይም ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋን አሽከርካው **ወይም ባለንብረቱ ወይም ተጎጂው** ወይም አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠው ወገን ወይም ፖሊስ ወይም ትራፊክ ፖሊስ ወይም ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ወዲያወኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. የመድን ፈንድ ክፍያዎች አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2004 ንዑስ ቁጥር 8 ላይ አደጋን ስለማሳወቅ በተገለፀው መሠረት ለኤጀንሲው ዋና መ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ላለው የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ወይም በኤጀንሲው ለተወከለ መድን ሰጪ ወይም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ለሰጠው ተቋም ወይም ለተጎጂው ሕጋዊ ተወካይ በማሳወቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

3. አደጋውን የሚያሳወቀው በኤጀንሲው የተመዘገበ ትክክለኛ አድራሻ ሲሆን፤ በስልክ፣ በፋክስ ወዘተ ወይም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው መድን የሌለው ወይም ያልታወቀ ተሽከርካሪ የአደጋ ማሳወቂያ ወይም የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማጠየቂያ ቅጽ ማስረት ሊሆን ይችላል፡፡

## 8. ከግዴታ ነፃ የሆነ ተሽከርካሪ

1. በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ መድን ከመግዛት ድንጋጌ ነፃ የሆነ ተሽከርካሪ ስላደረሰው አደጋ ባለንብረቱ ወይም ተቋሙ ወይም አሽከርካሪው ወይም ፖሊስ ወይም ትራፊክ ፖሊስ ወይም ሌላ የሚመለከተው ማሳወቅ አለበት፡፡
2. አደጋውን የማሳወቂያ መንገድ ኤጀንሲው ወይም በኤጀንሲው የተወከለው ሰው ~~አካል~~ በሚያወጣው ቅጽ ወይም በስልክ፣ በፋክስ ወዘተ ይሆናል፡፡

## 9. የአደጋ መረጃ አሰባሰብ

1. በአዋጁ አንቀጽ 11 ማሰረት ሚጃ ማስጠትን በተማከተ ሚን ገቢው የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ተጎጂው ወይም መብት ያለው ወገን ሲጠይቅ ተሽከርካሪው ሚን ያለው ወይም የሌለው ማሆኑንና የሚን ማስክር ወረቀቱ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 9 የተማከቱትን ሁኔታዎች በማገለጽ ሚጃ የማስጠት ግዴታ አለበት፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 13 የሚን ተለጣፊ አለማዝ የሚን ሽፋን እንደሌለው ስለማያስቆጥረው የሚን የማስክር ወረቀት እስኪማጣ ድረስ ፖሊስ ይዞ እንዲያቆየው ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

3. በኤጀንሲው የተዘጋጀውና በትራፊክ ፖሊስ የህክምና ተቋሙ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ የሚተላለፈው የማጠየቂያ ቅጽ እንደ አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ እና የአደጋ ሚጃ ምንጭ ሊወሰድ ይችላል ፡፡

4. የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ማጠየቂያ ቅጽ ሞር ሚን ላላቸው ወይም ሚን ለሌላቸውና ላልታወቁ እንዲሁም ከአዋጁ ድንጋጌ ነፃ ለተደረጉ ተሽከርካሪዎች በሙሉ አደጋ ለማሳወቅና ክፍያ ለማጠየቅ የሚያስፈልጉ ሚጃዎችን በማስጠት ያገለግላል፡፡

## 10. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት

1. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ማሰረት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው እስከ ብር 2,000.00 ድረስ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 2 ማሰረት ማንኛውም የህክምና ተቋም የተሽከርካሪ አደጋ ደርሶበት ወደ ህክምና ተቋም ለመጣ ማንኛውም ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የማስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠ የህክምና ተቋም ለአገለልግሎቱ ያወጣውን ወጪ በዚህ መሚያ ላይ በተገለጸው ማሰረት እንዲከፈለው ማጠየቅ ይችላል፡፡

## 11. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ዓይነት

1. የአስቸኳይ ህክምና የሚከተሉትን አገልግሎቶች ያካትታል፡-

ሀ. በአደጋው ቦታ የሚደረግ የማጀሚያ ደረጃ ህክምና፤

ለ. ከአደጋው ቦታ ወደ ህክምና ተቋማት ተጎጂው በሚወሰድበት ወቅት የተሰጠ የአምቡላንስ አገልግሎትና በጉዞው ወቅት የሚደረግ የህክምና አገልግሎት እንዲሁም፣

ሐ. በህክምና ተቋም የድንገተኛ ክፍል ወስጥ በባለሙያ የሚሰጥ የነፍስ አድን የህክምና አገልግሎት ሲሆን፣አገልግሎቱ የሚከተሉት ሶስት ቦታዎች ላይ ~~አገልግሎቱ~~ ሊሰጥ ይችላል፡ -

1. የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ በባለሙያ ነርስ የሚደረግበት ቦታ (The triage area)፤

2. የተለያዩ የነፍስ አድን ሥራዎች የሚከሄደበት ቦታ (The resuscitation area)

3. በድንገተኛ ክፍል በሚገኝ ተሽከርካሪ ጎማ ያለው አልጋ (Gurney) ወይንም ተጎታች ጋሪ (Trolley) ተጎጂው የሚያርፍበት ቦታ "The major or general medical area"

2. ከላይ የተገለጹት የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አይነቶች በሙሉ በአንድ የህክምና ተቋም ወይንም በተለያዩ የህክምና ተቋማት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ የህክምና ተቋም እንደሰጠው አገልግሎት ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

3. በድንገተኛ ክፍል ለተጎጂው ህክምና እየሰጠ ያለው የሕክምና ባለሙያ ልዩ ህክምና እንዲያገኝ ወይም በህክምና ተቋሙ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት እንዲታከም ወሳኔ ሲሰጥ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎቱ ያበቃል፡፡

4. በአዋጁ መሰረት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ወጪ ከአካል ጉዳት እና ከሞት ጉዳት ካሣ ላይ ተቀናሽ አይደረግም፤ ወይም በጉዳት ካሣ ስሌቱ ወስጥ አይካተትም፡፡

## 12.በአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ወስጥ የሚይካተቱ ጉዳዮች

1. የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አጠቃላይ ወጪ ከብር 2,000.00 በላይ ከሆነ ልዩነቱን የተሸከርካሪው ባለንብረት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ልዩነቱን ይከፍላል ፡፡

2. ተጎጂው የላቀና ልዩ የህክምና አገልግሎት ወይም በህክምና ተቋም ወስጥ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት በመታከሙ ምክንያት የመጣ የህክምና ወጪ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ስላልሆነ ከሌሎች የጉዳት ዓይነቶች ማለትም የአካል ጉዳት ወይም የሞት ካሣ ላይ ተቀንሶ ይከፈለዋል፡፡

3 በዚህ አንቀፅ ንዐስ አንቀፅ (2) ላይ የተገለፀወን የህክምና ወጪ በሚከተሉት ወገኖች የሚሸፈን ይሆናል፡ -

ሀ) መድን ባላቸው ተሽከርካሪዎች በደረሰ አደጋ የመጣ ጉዳት ከሆነ የመድን ሽፋኑንና የምስክር ወረቀቱን በሰጠው የመድን ሰጪ ከባንያ፣

ለ) መድን በሌለወና ባልታወቀ ተሽከርካሪ አደጋ የደረሰ ጉዳት ከሆነ በኤጀንሲው፣

ሐ) በአዋጁ መሠረት የሶስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ሽፋን እንዲገቡ በሚይገዱ ተሽከርካሪዎች የደረሰ ጉዳት ከሆነ ህጋዊ ወክልና በተሰጠው አካል፤

4.ሌላ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ከአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ውጭ ለሚደረግ ሕክምና ወጪ ከሌሎች የጉዳት ካሳ ክፍያዎች ጋር ተደምሮ በአዋጁ አንቀጽ 16(1) ላይ ከተገለጹት የኃላፊነት ማጠን በላይ የሚድን ወል የሰጠው ኩባንያ ወይንም ኤጀንሲው የመሸፈን ግዴታ የለባቸውም፡

5.በአዋጁ **አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (1)** እና **(2)** ላይ ከተቀመጠው ኃላፊነት በላይ ለሚሄጡ ማንኛውም ዓይነት የጉዳት ካሳዎች የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ኃላፊነት የተጣለበት ወገን የሚሸፈን ወይም የሚከፈል ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

### የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀምና ተፈላጊ ሚጃዎች

**13 የአገልግሎት ክፍያ ስለማጠየቅ**

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ማንኛውም የህክምና ተቋም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ ሊጠይቅ የሚችለው በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ለተሰጠ የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት ብቻ ነው፡
2. በሕክምና ተቋም የሚሰጠው የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሚፈፀም አለበት፡፡
3. ማንኛውም አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የሰጠ የህክምና ተቋም ክፍያ ሊጠይቅ የሚችለው የሚከተሉትን አካላትን ነው ነው፡-
   ሀ. በዘጠኙ ክልሎች የሚገኙ የጤና ተቋማት በሚገኙበት ክልል ያለውን "የወረዳ ጤና ጽ/ቤት"ን ፤
   ለ. በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የጤና ተቋማት በመሚገኙበት ከተማ "የአስተዳደሩን የጤና ቢሮ"ሲሆን እንደአግባብነቱ ጤና ቢሮዎቹ ከኤጀንሲው ጋር በሚያደርጉት ስምምነት ከዚህ የተሻለ አሰራር ተግባራዊ ሊደርጉ ይችላሉ፡፡

**14 ክፍያ ለማጠየቅ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ**

አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ተቋም ለሰጠው አገልግሎት ክፍያ ሲጠይቅ፤

1. በዚህ መመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ ማከተል፣
2. በዚህ መመሪያ መሠረት የተዘጋጀውን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ ማጠየቂያ አባሪ እና ሌሎች የተገለፁ ቅጾችን (የትራፊክ ፖሊስ፣ የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ማጠየቂያ ቅጽ ወዘተ…) እንዲያያዝ ማድረግ፣
3. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሚጃዎችን ማጠናቀርና ተጎጂው ህክምና በሚያገኝበት ድንገተኛ ክፍል ወስጥ በግልጽ ሊታይ በሚችል ቦታ በሚለጠፍ ፖስተር ላይ ይጻፋል፡፡

ሀ. የተጎጂወን ስምና ሙሉ አድራሻ ፣

ለ. ተጎጂው በተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ መሆኑን በሚገኙ ሚጃዎች በማገራት የአደጋወንቦታ፤ ቀንና ሰዐት ፣ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር፣

ሐ. ለአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተጎጂወን ወደ ህክምና ተቋሙ የላከወን ትራፊክ ፖሊስ፤ ፖሊስ ወይም ግለሰብ ስምና ሙሉ አድራሻ ፣ የትራፊክ ፖሊስ ከሆነ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማጠየቂያ ቅጽ እንዲቀርብ ማድረግና ማያያዝ፣

መ አደጋው የደረሰው መድን በገባ ተሽከርካሪ ከሆነ የመድን ሰጪው ኩባንያው ስምና የመድን የምስክር ወረቀት ቁጥር ፣

ሠ. አደጋው የደረሰው መድን በሌለው ተሽከርካሪ ከሆነ የተሽከርካሪወን ባለቤት ወይም የአሽከርካሪወን ስምና አድራሻ እንዲሁም የተሽከርካሪወን የሰሌዳ ቁጥር ፣

ረ. አደጋው የደረሰው ባልታወቀ ተሽከርካሪ ከሆነ ጉዳዩን የመዘገበው የትራፊክ ፖሊስ ወይንም ወደ ህክምና ተቋሙ ያመጣወን ሰው ስምና አድራሻ፣

4. አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ በማጠየቂያ ቅጽ ተሞልቶ እና በሕክምና ተቋሙ ኃላፊ ተፈርሞ ለተጎጂው የተሰጠወን አገልግሎትና የወጪ ዝርዝር ከተፈላጊ ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ጋር በአግባቡ በመሟላት በአባሪነት ማያያዝና ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከማስረጃዎቹ መካከልም እንደአግባብነቱ፤ዋና ነው ወይ

ሀ.የሀኪም ትዕዛዝ፣ የሀኪም የምስክር ወረቀት፣ ደረሰኝ የመድሀኒት ወይንም የላብራቶሪ ምርመራ ክፍያና ሌሎች ሰነዶችን ጭምር ያካትታል፡፡

ለ.የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት፣ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማጠየቂያ ቅጽ፣ የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ክፍያ ማጠየቂያ ቅጽ እና የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት ዋንኞቹ ናቸው፡፡

## 15. የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ አቀራረብና የአፈፃፀም ሥርዓት

1. ማንኛውም የሕክምና ተቋም አገልግሎት የሰጠበት ወር በተጠናቀቀ በ10 ቀን ወስጥ በዚህ መመሪያ በተዘረዘረው መሠረት በቁጥር 13 (3) ለተመለከተው አካል የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
2. የክፍያ ጥያቄወና አባሪ ሰነዶች የሚቀርበት ለዚሁ ተግባር ተብሎ በተሰራጨው የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ክፍያ ማጠየቂያ ቅጽ ላይ አስፈላጊ ሚጃዎች ተሞልተወና በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ የሕክምና ተቋሙ ማህተምና የኃላፊው ፊርማ እንዲያርፍበት ተደርጎ ነው፡፡

3. ከተገለፀው የ10 ቀን የጊዜ ገደብ ከአልፈ በኋላ በተንጠበጠበ መንገድ የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎችና አባሪ ሰነዶች ሊስተናገዱ የሚችሉት በሚቀጥለው ወር ይሆናል፡፡

4. የአገልግሎት ክፍያ በአካባቢው ከሚገኙ የህክምና ተቋሞች የቀረበለት በክልል የሚገኝ የወረዳ ጤና ቢሮ አስፈላጊውን ማጣሪያ ካደረገ በኋላ በሸኚ ደብዳቤ ሰነዶቹ በደረሱት በ10 የሥራ ቀን ውስጥ ክፍያው አገልግሎት በሰጠው ተቋም ስም እንዲፈፀም ለክልሉ የጤና ቢሮ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

5.የወረዳው የጤና ጽ/ቤት የሚያደርጋቸው ማጣሪዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ.የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄውና በአባሪነት የተያያዙት ሰነዶች ትክክለኛነት፣

ለ. የክፍያው ጥያቄ አቀራረብ በዚህ መመሪያ ላይ በተዘረዘረው መሠረት እንደሆነ እና

ሐ.የቀረበው የክፍያ ጥያቄ በዓመቱ ውስጥ ከተስተናገዱ የክፍያ ጥያቄዎች ጋር ተደምሮ በወረዳው ለሚገኙ የጤና ተቋማት በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በጥቅል ከተመደበው የተዘዋዋሪ ፈንድ የሚበልጥ መሆኑን ነው፡፡

6. አጠራጣሪ እና ያልተሟላ መረጃ ያላቸውን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የክፍያ ጥያቄዎችን ደግሞ ሁኔታውን ዘርዝሮ በመግለጽ ሰነዶቹን ለሚመለከተው የህክምና ተቋም ውዲያውኑ በሸኚ ደብዳቤ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

7. በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ ከተማ ያሉ የአስተዳደር ጤና ቢሮዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በአስተዳደሩ ክልል በሚገኙ የሕክምና ተቋማት የቀረበላቸውን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄና አባሪ ሰነዶች በማጣራት ተገቢውን ክፍያ በ20 የሥራ ቀን ውስጥ ሚፈፀም ያለባቸዉ ሲሆን፣

ሀ. የሚጣሩት ጉዳዮች ከላይ በ15 (5)የተገለፁት ተግባሮች ናቸው፡፡

ለ. አጠራጣሪና ያልተሟላ መረጃ ያላቸው የክፍያ ጥያቄዎች ለሚመለከተው የጤና ተቋም በሸኚ ደብዳቤ አማካኝነት በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ መላክ አለባቸው፡

## 16.የክልል/የከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ

የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ ከተለያዩ የህክምና ተቋማት የቀረበለትን የአገልግሎት ክፍያ በፈፀመ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ተገቢ የሆኑ ሰነዶችን በሙሉ በማያያዝ በሸኚ ደብዳቤ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

## 17.የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የአገልግሎት ክፍያ የተፈፀመባቸው ሰነዶች በደረሱት 10 የሥራ ቀናት ውስጥ በማጣራትና በመለየት ለሚመለከታቸው አካላት ማለትም ለሚመለከተው የመድን ሰጪ ኩባንያ ወይንም ለመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ይልካል፡፡

## 18.የሩብ ዓመት ሪፖርት ስለመላክ

-7.4.1

1. በክልል የሚገኝ የወረዳ ጤና ተቋም የሩብ ዓመቱ ባለቀ በ10 ቀናት ውስጥ የተፈፀመ የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት አጠናቅሮና አዘጋጅቶ ለክልሉ የጤና ቢሮ መላክ አለበት፡፡
2. የክልሉ የጤና ቢሮ በየሩብ ዓመቱ የተከፈሉ የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት ከየወረዳዎቹ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ በሚደራጀት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

**19.በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች**

በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የጤና ተቋማት የተፈፀመውን የአገልግሎት ክፍያ ሚዛን የያዘ ሪፖርት በማጠናቀርና በማዘጋጀት የአስተዳደሩ ጤና ቢሮ የሩብ ዓመቱ ባለቀ በ20 ቀናት ውስጥ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

**20.የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሩብ ዓመቱ ባለቀ በ30 ቀናት ውስጥ ከክልልና ከሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች የጤና ቢሮዎች የተላከለትን የሩብ ዓመት የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት ለኤጀንሲው ይልካል፡፡

ኤጀንሲው

**ሀ.** ኤጀንሲው የሩብ ዓመት የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት ተጠቃሎ በደረሰው በ10 ቀን ውስጥ በክልልና በከተማ አስተዳደር የተደረገውን የክፍያ አፈፃፀም ከተያዘው የተዘዋዋሪ ፈንድ ጋር የሚነፃፀር አጠቃላይ ሪፖርት በማቅነባበርና በማዘጋጀት ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

**ለ.** በተለይም በሁለተኛው ሩብ ዓመት ሚጨረሻ አጠቃላይ የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት በሚያጠናቅርበት ወቅት በአንደኛውና በሁለተኛው የሩብ ዓመት የክፍያው ማጠን በስሌት ከተገመተው የተዘዋዋሪ ፈንድ ጋር ሲነፃፀር 3/4ኛ ወይም 75% ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን ሚዛኖች ከጠቆሙ ለቀረው ዘመን የሚሆን ማስተካከያ የተዘዋዋሪ ፈንድ ማጠንና እያንዳንዱ የሚያላከተው ወገን የመዋጮ ድርሻውን ያሳውቃል፡፡

**ሐ.** በሶስተኛው ሩብ ዓመት ተከታታይ የሩብ ዓመት የአገልግሎት ክፍያዎች ከተያዘው የፈንድ ተመን ሲነፃፀር 3/4 ወይም 75% ሆኖ ከተገኘ በተመሳሳይ መንገድ ለቀሪው ጊዜ የሚያስፈልገውን የፈንድ ማጠንና ሚያላከታቸው ወገኖች የመዋጮ ድርሻቸውን ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር

## የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ

### 21.መቋቋም

የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ከዚህ በኋላ ተዘዋዋሪ ፈንድ እየተባለ የሚጠራ የገንዘብ ምንጭ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡

### 22.የተዘዋዋሪ ፈንዱ ዓላማ

የተዘዋዋሪ ፈንዱ ዓላማ በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 27 የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

### 23.የተዘዋዋሪ ፈንዱ ምንጭና የማጠን ስሌት

1.የተዘዋዋሪ ፈንዱ የገንዘብ ምንጭ

የተዘዋዋሪ ፈንዱ ከመድን ሰጪ ኩባንያዎችና ከመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የሚሰበሰብ ዓመታዊ መዋጮ ነው፡፡

**8.1. --የመድን ሰጪ ኩባንያዎች የመዋጮ ድርሻ**

2.የእያንዳንዱ የመድን ሰጪ የመዋጮ ድርሻ የሚወሰነው በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በፌዴራል ፖሊስ ባለፈው ዓመት በተሰበሰበ የትራፊክ አደጋ መረጃን፣ በኩባንያዎቹ የተሽከርካሪ መድን የገበያ ድርሻ ማለትም በመድን የምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ አጠቃቀም ላይ ተመርኩዞ የሚሰላ ይሆናል፡፡

3.የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የመዋጮ ድርሻ

የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የመዋጮ ድርሻ የሚወሰነው በተመሳሳይ ሁኔታ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ከፌደራል ፖሊስ በተሰበሰበ ያለፈው ዓመት የትራፊክ አደጋ ሲሆን በስሌቱ ወቅት፡ -

ሀ.ባልታወቁ ተሽከርካሪዎች የደረሱ አደጋዎችና የተጎጂዎች ቁጥር እንዲሁም፣

ለ.መድን በሌላቸው ተሽከርካሪዎች ሊደርሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ አደጋዎችና የተጎጂዎች ቁጥር ለዚሁ ተብሎ በሚሰበሰብ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 24.የመዋጮ ማጠንና ድርሻ የሚወሰንበት ጊዜ

የተዘዋዋሪ ፈንዱ ማጠንና ገቢ የሚሆነው የመዋጮ ድረሻ በየዓመቱ ባለ የመጀመሪያ ወር ላይ ሆኖ ኤጀንሲው በሚያደርገው ጥናት ላይ ተመርኩዞ ቦርዱ በሚወስነዉ ማስረት ነው፡፡

## 25.የመዋጮ ማጠንና ድርሻ ስለማሳወቅ

ኤጀንሲው በዚህ ማንገድ የተሰላውን የተዘዋዋሪ ፈንድ ማጠንና የመዋጮ ድርሻ ቦርዱ ወሰኔ በሰጠ በ24 ሰአት ወስጥ ለሚሟከተው አካል በጽሐፍ ያሳውቃል፡፡

## 26.የተዘዋዋሪ ፈንድ የመዋጮ ድርሻ

1.በተዘዋዋሪ ፈንድ የመዋጮ ድርሻ ገቢ የሚደረጉ ክፍያዎች ተቀማጭ የሚሆነው ለዚሁ ተብሎ በጤና ጥበቃ ሚ/ር በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ወስጥ ነው፡፡

2.በአንቀፅ 24 የተሰላው ዓመታዊ የመዋጮ ድርሻ ለተዘዋዋሪ ፈንዱ በተከፈተው የሂሳብ አካወንት ወስጥ በተጠቀሱት አካላት ከዚህ በታች በተገለጹት የሩብ ዓመት የመጀመሪያ ወራት ላይ ቀጥሎ እንደተማከተዉ ገቢ ሟድረግ አለባቸው፡-

| | |
|---|---|
| ሀ. አንደኛ /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት | ከመስከረም 25 - 30 |
| ለ. ሀለተኛ ሩብ ዓመት | ከታህሳስ 25 - 30 |
| ሐ. ሶስተኛ ሩብ ዓመት | ከመጋቢት 25 - 30 |
| መ. አራተኛ ሩብ ዓመት | ከሰኔ 25 - 30 |

3.በተጠቀሱት የክፍያ ወቅቶች ወስጥ የሚደርስበትን መዋጮ ገቢ ያላደረገ አካል ክፍያው ላዘገየበት ጊዜ ከመዋጮው በተጨማሪ በወቅቱ ባለ የባንክ ወለድ የሚሰላ ቅጣት እንዲከፈል ይደርጋል፡፡

4.የመዋጮ ክፍያወን የማዘገየቱ ተግባር ገቢ ሟድረግ ከአለበት ጊዜ ከሁለት ወር በላይ ከሆነ ወይንም ከሁለት ወር ላነሰ ጊዜ ሆኖ ከሶስት ጊዜ በላይ የተፈፀመ ተደጋጋሚ ጥፋት ከሆነ አጥፊው ወገን በአዋጁ አንቀጽ 30 መሠረት ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 27.የተዘዋዋሪ ፈንዱ ሥርጭት

1.በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ የሆነው የተዘዋዋሪ ፈንዱ መዋጮ ባለፉት ዓመታት ከፌዴራል ፖሊስ በተሰበሰበ የትራፊክ አደጋ ሚኒጃ ላይ ተመርኩዞ በሚደረግ ስሌት መሠረት ለዘጠኝ ክልል እና ለሁለት የከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች ይከፋፈላል፡፡

2.በዚህ ማንገድ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች ተሰልቶ የሚመደበው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ ተቀማጭ የሚሆነው በሚመለከተው የጤና ቢሮ ስም ለዚሁ ተብሎ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ነው፡፡

3.በክልል እና በከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ወስጥ ገቢ የሚሆነው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ በክልሉ ወይንም በከተማ አስተዳደሩ ሥር ባሉ ወረዳዎች ደርሰዋል ተብለው በተማዘገቡና በክልሉ ወይንም በፌደራል ፖሊስ ከተሰበሰቡ የትራፊክ አደጋዎች እና በተጎጂዎች ቁጥር ላይ ተመርኩዞ በማከላት ለየወረዳዎቹ የሚመደብ ሲሆን፣

ሀ. በክልል ለሚገኙ የወረዳ የጤና ፅ/ቤቶችና የተሰላው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ ገቢ ወይም ተቀማጭ የሚሆነው በሚመለከተው ክልል ጤና ቢሮ ስም ለዚህ ጉዳይ ተብሎ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ነው፡፡

ለ. በእያንዳንዱ ወረዳ ሥር ባሉ የሕክምና ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም በክልሉ ጤና ቢሮ የባንክ ሂሳብ ለወረዳው ለወቅቱ በታሳቢነት ከተያዘለት ወይም ከተመደበለት ገንዘብ ይቀንሳል፡፡

ሐ. እያንዳንዱ ወረዳ በዚያ ዓመት በተጠባባቂነት ከተያዘለት ወይም ከተመደበለት የፈንድ ድርሻ በላይ ለማጠቀም የክፍያ ጥያቄ ከቀረበ ጉዳዩን የክልሉ የጤና ቢሮ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

መ. የጤና ጥበቃ ሚ/ር የጋራ ኮሚቴወና በኤጀንሲው ወሳኔ መሠረት የአገልግሎት ክፍያው ጥያቄ ይስተናገዳል፡፡

**28.**ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለክልል ወይንም ለከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች የሚሰራጨው እንዲሁም በተዋረድ ከክልልና ከከተማ አስተዳደር የጤና ተቋማት ለወረዳ ጤና ቢሮዎች በታሳቢነት የሚያዘው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ የሚወሰነው ኤጀንሲው የተዘዋዋሪ ፈንዱን ማጠን ለማከላት በየዓመቱ ከሚያደርገው ጥናት ጋር በአንድነት ሲሆን የሚወሰነውም በቦርድ ነው፡፡

**29.የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመላ ከአገልግሎት ክፍያ ማነስ**

1. በአጠቃላይ ለዓመቱ ሊበቃ ይችላል ተብሎ የተሰላው የተዘዋዋሪ ፈንድ ማጠን በጥቅሉ አንሶ ሲገኝ ተጨማሪ የመዋጮ ክፍያ በሚመለከታቸው አካሎች ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

2. የተጨማሪ አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመኑ ማጠን ከዚህ እንደሚከተለው ይሰላል፡፡

$$\frac{\text{ለዓመቱ የተተመነው አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ የገንዘብ ማጠን}}{\text{365 ቀናት}} \times \text{ያሉ ቀሪ ቀናት}$$

3. በዚህ ማንገድ የተሰላው አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመን ማጠን በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለስሌት በተወሰዱ ማከያዎች ማለትም የመድን ምክክር ወረቀትና የመድን ተለጣፊ አጠቃቀም ብዛት፣ መድን የሌላቸውና ያልታወቁ ተሸከርካሪዎች ግምታዊ ብዛት ላይ ተመስርቶ ለሚሟከተው ለእያንዳንዱ አካል የመዋጮ ድርሻ ይተመናል፡፡

4. የተተመነው ተጨማሪ የተዘዋዋሪ ፈንድ ማጠንና ድርሻ እንዲሁም ስርጭት በቦርድ በተፈቀደ በ24 ሰአት ወስጥ ለሚሟከታቸው አካላት ኤጀንሲው በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

5. የዚህን የመዋጮ ድርሻ ኤጀንሲው በደብዳቤ ባሳወቀ በ10 ቀናት ወስጥ ለዚሁ በተከፈተው የጠፍ ጥበቃ ሚኒስቴር የሂሳብ ቁጥር ወስጥ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

## 30.የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመኑ ከአገልግሎት ክፍያ ሲበልጥ

1. ለዓመት እንዲሆን የተሰላዉ የተዘዋዋሪ ፈንድ ኦዲት ከተደረገ በኋላ ትርፍ ከተገኘ ለሚቀጥለው ዓመት እንዲንከባለል ይደረጋል፡፡

2. የሚንከባለለው በትርፍ የተያዘ ተዘዋዋሪ ፈንድ ማጠን ለዓመቱ ከሚሰላው ተመን ላይ ተቀናሽ ስለሚሆን የሚሟከታቸው አካላት በእያንዳንዳቸው ለመጪው ዘመን ከሚዋጡባቸው የመዋጮ ድርሻ ላይ በዚሁ ትርፍ ማጠን እንዲቀንስላቸው ይደረጋል፡፡

## 31.የተዘዋዋሪ ፈንድ የሂሳብ ዘመን

የተዘዋዋሪ ፈንዱ የሂሳብ ዘመን በየዓመቱ ከመስከረም 1 ቀን በመጀመር እስከ ጳጉሜ 5/6 ድረስ ይሆናል፡፡

## 32.ኦዲት ስለማስደረግ

1. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ዓመቱ ባለቀ የመጀመሪያው ወር ላይ ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡

2. የኦዲት ሪፖርቱ ለሚሟከታቸው አካላት እንዲሁም ለቦርድ ቀርቦ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የባለድርሻ አካላት በተገኙበት የጋራ ወይይት ይደረግበታል፡፡

3. የኦዲት ሪፖርቱ ለሚመጪው ዘመን የተዘዋዋሪ ፈንድ ትመናና የአገልግሎት ክፍያ እንዲሁም ሌሎች ተግባራት መሠረታዊ ግብዓት በመሆን ያገለግላል፡፡

# ክፍል አራት

## የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ

### የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አደረጃጀትና ኃላፊነት

**33.የጋራ ኮሚቴው አወቃቀር**

**1.**የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያወን ተግባራዊነት የሚያረጋግጥ እና የሚቆጣጠር የጋራ ኮሚቴ በሚከተሉት አካላት በሚውከል አራት አባላት ይቋቋማል፡ -

ሀ. መድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ፡ - ሰብሳቢ

ለ. ጠና ጥበቃ ሚኒስቴር ፡ - ጸሐፊ

ሐ. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ፡ - አባል

መ. የመድን ሰጪ ኩባንያዎች ፡ - አባል

**2.**የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ይሆናል፡፡

**3.**በተለያዩ ምክንያቶች ከጋራ ኮሚቴው አባል ሲወጣ በጎደለው አባል ምትክ የሚተካከተው ወገን በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ መተካት አለበት፡፡

**34. የኮሚቴው የግንኙነት ጊዜ**

1. የጋራ ኮሚቴው በተቋቋመ በአንድ ወር ወስጥ ለአገልግሎቱ ዘመን የሚሆን የስራ እቅድና መርሃ ግብር በማውጣት ለኤጀንሲው ያቀርባል፡፡

2. ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው በመደበኛነት በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ነገር ግን እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህ ባነሰ ጊዜ በማሰብሰብ ሥራውን በማከናወን የተጣለበትን ኃላፊነት ይወጣል፡፡

**35. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት**

ኮሚቴው ከዚህ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡ -

1. በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች በዚህ መመሪያና በአዋጁ መሰረት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን ይገመግማል፣
2. በአሰራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በመገምገም ማስተካከያ ዕርምጃ መወሰድ እና ከኮሚቴው አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችን ለኤጀንሲው ያቀርባል፣
3. ለአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የተመደበው ገንዘብ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ በተዘረዘረው መሰረት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተገኙ ውጤቶችን በየሩብ ዓመቱ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያቀርባል፣
4. ከኤጀንሲው ጋር በመሆን የተዘዋዋሪ ፈንድ ማጠን ትመናና ማስተካከያ ጥናት ለቦርድ ከመቅረቡ በፊት ይመረምራል፣
5. በየዓመቱ የተዘዋዋሪ ፈንድ ሂሳብን ኦዲት ያስደርጋል፤ ወጤቱንም በመገምገም ከኤጀንሲው ጋር በመሆን ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

**36. የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ**

1. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የክፍያ ማጠየቂያ ቅጽ በማተም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ለህክምና ተቋማት ያከፋፍላል፣
2. የተዘዋዋሪ ፈንድ ማጠንና ድርሻ በማጥናት ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲወሰንም ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ያሳውቃል፣
3. የተዘዋዋሪ ፈንድ የማዋጣት ግዴታ ያለባቸውን አካላት መክፈል ያለባቸውን የአስተዳዳሪያዊ ወጪ ድርሻ በማስላት በየሦስት ወሩ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲወሰንም ለጤና ጥበቃ ሚ/ር እንዲከፍሉ በማሳወቅ ያረጋግጣል፣
4. ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አንድ ተወካይ ይመድባል፣
5. የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የማጠየቂያ፣ የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት ማስጫ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችንና ቅጾችን በማዘጋጀትና በማተም ያሰራጫል፣
6. የሩብ አመትና ሌሎች ሪፖርቶችን የአገልግሎት ክፍያ ሚዛን የሚያዝበት የባሕር መዝገብ ያዘጋጃል፣ ሌሎች ለኦዲት ስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በአግባቡ በማስቀመጥ እንደአስፈላጊነቱ ያቀርባል፣

**37. የመድን ሰጪ ኩባንያዎች**

1. እያንዳንዱ የመድን ሰጪ ኩባንያ ለአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ የሚሆን መዋጮ (ለተዘዋዋሪ ፈንድ የሚከፈል ድርሻ) በየሩብ አመቱ በጤና ጥበቃ ሚ/ር ስም በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደርጋል፡፡
2. የመድን ሰጪ ኩባንያ በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደረገውን ገንዘብ ማጠን የሚያሳይ የባንክ አድቫይስ ኮፒ ለኤጀንሲው መላክ ወይም ማሳወቅ አለበት፡፡
3. ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አንድ ተወካይ ይመድባል፡፡

**38. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

1. በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሰረት ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት ክፍያ የሚሆን መዋጮ የሚሰበሰብበትን ተዘዋዋሪ ፈንድ የሚቀመጥበትን የባንክ ሂሳብ በመክፈት ቁጥሩን ያሳውቃል፣ ለክልልና ለከተማ አስተዳደሮች የጤና ቢሮዎች ይደለድላል፣ ያስተዳድራል፣

2. በዚህ መመሪያ ከተካተቱ ጉዳዮች እንደአስፈላጊነቱ ስለተመደበው ገንዘብ አጠቃቀም፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የሪፖርት አቀራረብ እና የደጋፊ ሰነድ አቀራረብ የአሰራር መመሪያ ከኤጀንሲው ጋር በጋራ ያወጣል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፣

3. ሚስቴሩ የሚያስተባብራቸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት አሰራሩን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር ከኤጀንሲው ጋር በጋራ ይሰራል፣

4. በየሩብ ዓመቱ ስለሰራ አፈፃፀሙ የስራ ግምገማ ያደርጋል፣ ውጤቱንም ለባለድርሻ አካላት ከኤጀንሲው ጋር በመሆን ያቀርባል፣

5. የክልል የጤና ቢሮ የሕክምና ተቋማት የከፈሉት የአገልግሎት ክፍያ ማጠየቂያና አባሪ ሰነዶችን ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያስተላልፋል እንዲሁም ክፍያውን የሚገልጽ የሩብ ዓመት ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል፣

6. ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አንድ ተወካይ ይመደባል፡

**39.የጤና ቢሮ**

1. ከአሰቸኳይ ህክምና አገልግሎት ሰጪ የህክምና ተቋማት የተላከለትን የወጭ ሰነድ አጣርቶ በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ ክፍያ እንዲከፈል ያደርጋል፣

2. ከህክምና ተቋማት የተላከለትን የወጪ ሰነድ አጣርቶ ክፍያ ከፈጸመ በኋላ ሰነዶቹን ለጤና ጥበቃ ሚ/ር በወቅቱ ያስተላልፋል፣

3. ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትና የህክምና ተቋማት የዚህን መመሪያ ይዘት እንዲያወቁትና በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርጉት አስፈላጊውን ተግባር ይፈጽማል፣

4. የሩብ ዓመት የክፍያ አፈጻጸም መግለጫ ሪፖርት በማዘጋጀት ለጤና ጥበቃ ሚ/ር በዚህ መመሪያ ላይ በተገለጸው ጊዜ ይልካል፣

**40.የወረዳ ጤና ጽ/ቤት**

ከጤና ተቋማት የሚመጡ የአስቸኳይ ህክምና ጥያቄዎች አረጋግጦና ከጤና ቢሮ ጠይቆ ይከፍላል፡፡በተለይም -

**1. በስሩ □ሚ□ነዉ የሕክምና ተቋም** በመንገድ ላይ አደጋ ተጎጂ **ለሆነ ሰው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ አስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት□እንዲያገኝ በአዋጁ የተቀመጠዉን ድንጋጌና ይህን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርግ ይቆጣጠራል፣**

**2. አስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት በአደጋው ቦታ ወይም በአምቡላንስ በባለሙያ የሚደረግ ህክምና እና እንዲሁም በሕክምና ተቋም ውስጥ ባለ የድንገተኛ □ክል ዉስዓ ለተ□ጂዉ የሚደረግ የሕክምና አገልግሎት ወጭችን በሙሉ በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው የብር 2000 የአስቸኳይ የሕክምና ወጭ ይሸፍናል፡፡**

3. ታካሚው በሆስፒታል ወስጥ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት እንዲታከም የህክምና ባለሞያው ወሳኔ ሲሰጥ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎቱ ይቋረጣል፣ ቀጣዩ ህክምናን በተመለከተ ተጎጂው **እና** የጤና ተቋሙ ከመድን ፈንድ ወይም ከሌሎች መድን ሰጪዎች ጋር በማጋገር የሚቀጥል ይሆናል፣

**41. የሕክምና ተቋማት**

1. እስከ ብር 2000 ድረስ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣
2. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማጠየቂያ ቅጽ በመጠቀምና ሰነዶችን አባሪ አድርጎ በሚያዝ በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ ለህክምና ያወጡት ወጭ እንዲከፈላቸዉ ለወረዳ የጤና ጽ/ቤት ማቅረብ አለባቸው፣
3. በዚህ መመሪያ ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማስባሰብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**42. የፖሊስ ወይም የትራፊክ ፖሊስ**

1. ማንኛውም የትራፊክ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ተጎጂው ወደ ህክምና ተቋም እንዲሄድ ያደርጋል፣
2. የተሽከረካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ በቦታው ወይም በስፍራው የትራፊክ ፖሊስ ሳይኖር ተጎጂው ወደ ህክምና ተቋም የተወሰደ ከሆነ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ መድረሱን አጣሪቶ ለህክምና ተቋሙ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

**43. ሌሎች አካላት**

መድን የገባው ሰው፣ የተሸከርካሪው ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ፣ አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ፣ ስለአደጋው እንደሁኔታው ለኤጀንሰው፣ ወይም ለመድን ሰጭ ኩባንያው በ10 ቀን ወስጥ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

**44.ቅሬታ አቀራረብ**

1. ማንኛውም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት የህክምና ተቋም ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰው በዚህ መመሪያ በተገለጸው አሰራር መሰረት ባይፈጸምላትና ቅሬታ ቢኖረው ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ ወይም ለኤጀንሲው ማቅረብ ይችላል፤
2. የጋራ ኮሚቴው ወይም ኤጀንሲው የቀረበለትን ቅሬታ በማጣራት በ10 ቀናት ወሰጥ ምላስ ይሰጣል ወይም ሰፊ ጊዜ የሚያስፈልገው ከሆነ ተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ ምላስ የሚሠጥበትን ጊዜ

ያሳውቃል፡፡ይሁን እንጂ ማንኛውም ቅሬታ በቀረበ በ30 ቀናት ወስጥ አሜካቹ ሜስ ማንኘት ይኖርበታል፡፡

**45.የተጭበረበሩ ሰነዶችና የሀሰት የክፍያ ጥያቄዎች**

ማንኛውም አካል ለሚቀርበው ሀሰተኛ ሰነድ/ማስረጃ ወይም ለሚጠይቀው የሀሰት የክፍያ ጥያቄ አግባብ ባለው ሕግ ማስረት በወንጀልና በፍታብሄር ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**46.መመሪያን ስለ መሻር**

የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት በተመለከተ ከዚህ በፊት የወጣው የአስቸኳይ ህክምና አሰጣጥና ከጤና ተቋማት ጋር የሚኖረው የስራ ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

**47.መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህን መመሪያ የትራንስፖረት ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**48.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ወርቅነህ ገበየሁ

የትራንስፖርት ሚኒስትር

49.አባሪዎች

1. የድንገተኛ /አስቸኳይ/ ህክምና አገልግሎት መረጃ መስጫ ቅፅ - 1
2. የተሽከረካሪ አደጋ ሪፖርት ማሳወቂያ ቅፅ - 2
3. የድንገተኛ/ የአሰቸኳይ /ህክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ - 3
4. መድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ ማስታወቂ□ ቅ□ - 4 –
5. የካሣ ክፍያ አፈፃፀም ሪፓርት ቅጽ – 5 –
6. የካሳ ጥያቄ ማጠየቂያ ቅጽ – 6
7. የፈንድ ገቢ ማሰባሰቢያ ቅጽ –7 –
8. የተሽከርካሪ አደጋ ማስታወቂያ ቅጽ – 8 –
9. የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ሪፖርት ቅጽ 9

## ትራፊክ ፓሊስ
## የድንገተኛ /አስቸኳይ/ ህክምና አገልግሎት
## መረጃ መስጫ ቅጽ

ቀን ______________

№. 07501

1. የተጎጂው ሙሉ ስም ______________
2. የተሽከርካሪው አይነት እና ሰሌዳ ቁጥር ______________
3. የአሽከርካሪው ሙሉ ስም ______________
4. አደጋው የደረሰበት ቦታ /ቀን/ ሰዓት ______________
5. ተጎጂው የተላከበት የህክምና ተቋም ስም ______________
6. ትዕዛዙን የሰጠው የትራፊክ ፓሊስ ______________
   - ሙሉ ስም ______________
   - የፓሊስ ጣቢያው ስም ______________
   - አድራሻ፣ ክልል ________ ክ/ከተማ/ዞን ______ ወረዳ ______ ቀበሌ _____
     የስልክ ቁጥር ______________ ሞባይል ቁጥር ______________
   - ፊርማ ______________

<u>ማስታወሻ</u>፣ ይህ ቅጽ ለመድን ፈንድ ጽ/ቤት እንደ አደጋ ማሳወቂያ ያገለግላል
በ2 ኮፒ የሚዘጋጅ ሲሆን

- ✓ ዋናው ለህክምና ተቋሙ
- ✓ ቀሪው በትራፊክ ጽ/ቤት ይቀመጣል

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ይህ ቅጽ የደረሰው የጤና ተቋም ለተጎጂው የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ክፍያውን የሚመለከተውን አካል የመጠየቅ መብት አለው።

National Printing Press PLC

# የትራፊክ ፖሊስ

## የተሽከርካሪ አደጋ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

ቀን ______________

No. 2501

ለ ______________ (ሆስፒታል፣ ጤና ተቋም፣ ክሊኒክ)

ለ መድን ፈንድ ጽ/ቤት

1. አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ የሚታወቅ ከሆነ
   ሀ. ሙሉ ስም ______________
   ለ. መንጃ ፍቃድ ቁጥር ______ ደረጃው ______________
   ሐ. አድራሻ፣ ክልል ______ ክ/ከ/ዞን ______ ወረዳ ______ ቀበሌ ______ የቤት ቁጥር ______
   መ. የስልክ ቁጥር ______________ ሞባይል ቁጥር ______________
   ሠ. አደጋ አድራሹ አሽከርካሪ የማይታወቅ ከሆነ ይገለጽ ______________
2. አደጋ ያደረሰው ተሽከርካሪ የሚታወቅ ከሆነ
   ሀ. የሰሌዳ ቁጥር ______________
   ለ. የተሽከርካሪው ዓይነት ______________
   ሐ. የተሽከርካሪው ባለቤት
   - ሙሉ ስም ______________
   - አድራሻ፣ ከተማ/ክልል ______ ክ/ከተማ/ዞን ______ ወረዳ ______ ቀበሌ ______ የቤት ቁ. ______
     የስልክ ቁጥር ______________ የሞባይል ቁጥር ______________
   መ. የመድን የምስክር ወረቀት ቁጥር ______________
     የመድን ተለጣፊ ቁጥር ______________
     የመድን ውል ቁጥር ______________
     የውል ዘመን ከ ______________ እስከ ______________
     የመድን ሰጪ ኩባንያው ስም ______________
     ቅርንጫፍ ______________
3. የአደጋው መንስኤ ______________
4. የተሽከርካሪ አደጋው ዝርዝር መረጃ
   ሀ. አደጋው የደረሰበት ቀን ______________ ቦታ ______________ ሰዓት ______
   ለ. የአደጋው ዓይነት ______________
5. በደረሰው የተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ. | የተጎጂው ስም | ተሳፋሪ/መንገደኛ /ሾፌር/ ረዳት ወዘተ | የጉዳቱ ዓይነት (ቀላል/መካከለኛ /ከፍተኛ/ የሞት) | የተጎጂው አድራሻ | የተላከበት የህክምና ተቋም ስምና ስልክ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | |
| 2. | | | | | |
| 3. | | | | | |
| 4. | | | | | |

6. በደረሰው የተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት የደረሰበት ሌላ አካል ካለ ይገለጽ
   ______________
   ______________
7. በአደጋው የደረሰ የንብረት ጉዳት ______________
8. በፕላኑ መሰረት ተጠያቂ፡
   የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ______________ ሾፌር ______________
9. የመርማሪው ስም ______________
   የአደጋው መለያ ቁጥር ______________ የሞባይል ቁጥር ______________
   ስልክ ቁጥር ______________
   ፊርማ ______________

ማስታወሻ

ይህ ቅጽ በ 3 ኮፒ የሚታተም ሲሆን
- ዋናው ኮፒ ለመድን ፈንድ ጽ/ቤት/ለሚመለከተው የመድን ኩባንያ
- ሁለተኛው ኮፒ ለህክምና ተቋም
- ቀሪው ለፓሊስ

National Printing Press PLC

# የድንገተኛ /አስቸኳይ/ የህክምና አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ

ቀን ______________

No. 5001

- ይህ ሪፓርት የሚሞላው በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት የድንገተኛ /አስቸኳይ/ ህክምና በሰጠ የህክምና ተቋም ነው።
- ይህ ሪፓርት የሚሞላው የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ለህክምና ተቋሙ ካቀረበ በኋላ ነው።

1. የትራፊክ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ ሪፓርት
   - ሀ. የአደጋ መለያ ቁጥር ______________
   - ለ. የአደጋው መርማሪው ትራፊክ ፓሊስ
     - ስም ______________
     - መለያ ቁጥር ______________
     - ስልክ ቁጥር ______________ የሞባይል ቁጥር ______________
2. የታካሚው ዝርዝር መረጃ
   - ሀ. ስም ______________
   - ለ. ዕድሜ ______________
   - ሐ. ፆታ ☐ ወንድ ☐ ሴት
   - መ. አድራሻ
     - ክልል/ከተማ ______________ ክ/ከተማ/ዞን ______________ ወረዳ/ቀበሌ ______________ የቤት ቁጥር ______________
     - ስልክ ቁጥር ______________ ሞባይል ______________
   - ሠ. የጉዳት ዓይነት ቀላል የአካል ጉዳት /ከባድ የአካል ጉዳት/ሞት/
3. ታካሚው የተሰጠው የህክምና ዓይነት
   - ☐ በአደጋው ቦታ የተሰጠ የህክምና ዓይነት
   - ☐ የድንገተኛ የአምቡላንስ /የትራንስፖርት አገልግሎት
   - ☐ ህክምና ተቋም ድንገተኛ ክፍል የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት
   - ☐ በከፍተኛ ልዩ የህክምና እንክብካቤ ወይም ክትትል ክፍል
   - ☐ የተሰጠው የህክምና አገልግሎት ከላይ ከተገለጹት ውጭ ከሆነ እባክዎት ይግለፁት

________________________________________________

________________________________________________

4. የህክምና አገልግሎት በህክምና ተቋማት ውስጥ
   - ☐ ታካሚው በተመላላሽነት ታካሚ ነው።
   - ☐ ታካሚው በህክምና ተቋሙ ተኝቶ የሚታከም ነው።
     - ✓ ወደ ህክምና ተቋሙ የገባበት ቀን
     - ✓ በህክምና ተቋሙ የወጣበት ቀን
5. የክፍያ ጥያቄ

   የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርቡበት የህክምና አገልግሎት ዓይነትና የክፍያ መጠን ከዚህ በታች ይግለጹ፡-

| ተ.ቁ. | የህክምና አገልግሎት ዓይነት | የክፍያው መጠን | አባሪ ሰነዶች |
|---|---|---|---|
| 1. | | | |
| 2. | | | |
| 3. | | | |
| 4. | | | |

6. የህክምና ባለሙያውና የተቋሙ መረጃ፡-
   - ሀ. ስም ______________
   - ለ. የሙያ ደረጃ ______________
   - ሐ. የህክምና ተቋሙ ስም ______________
   - መ. አድራሻ ______________
   - ሠ. ስልክ ቁጥር ______________
   - ረ. የፋክስ ቁጥር ______________
   - ሰ. የህክምና ተቋሙ ኃላፊ
     - ስም ______________
     - ፊርማ ______________
     - የተቋሙ ማህተም

National Printing Press PLC

# መድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ

# የተሽከርካሪ አደጋ ማስታወቂ□ ቅ□ 4

**1. የተሽከርካሪ አደጋ ሪፖርት አድራጊው ሰው**

ስም:------------------------------------------

አድራሻ □ልል ----------------------------- ክ/ከተማ --------------------- ወረ□ --------------

ስ.ቁ : ---------------------------------------

**2.የአደጋው ሁኔ□**

ቀን : -------------------------- ሰዓት:- ----------------- ቦ□ ዉ: :- ------------

የአደጋው አይነት : -----------------------------------

**3.ጉዳት የደረሰባቸው ተጐጂዎች ዝርዝር፤**

ተቁ የተጎጂው ስም ተሳፋሪ/ማንገደኛ የጉዳቱ አይነት የተጎጂው አድራሻ ምርመራ

1: ---------------------- ---------------------- --------------------
---------------------- -----------------------

2: ---------------------- ---------------------- --------------------
---------------------- -----------------------

3: ---------------------- ---------------------- --------------------
---------------------- -----------------------

**2. የተደረገላቸው የሕክምና ዕርደ□ ካለ፤**

ተ.ቁ የተጎጂው ስም ክር□□ የሰጠው ተቋም ስም የተቋሙ አድራሻ ምርመራ

1----------------------- -------------------------------- -------
----------------- -------------------------

2----------------------- -------------------------------- -------
----------------- -------------------------

3----------------------- -------------------------------- -------
----------------- -------------------------

**5. አደጋ ያደረሰው ተሽከርካሪ ሁኔ□**

አደጋ ያደረሰው ተሽከርካሪ ይታወቅ ነበር ወይ? አዎ ☐ አይ□ ወቅም ☐

**5.1 ተሽከርካሪው ከ□ ወቀ**

□ሥሌ□ ቁዓሩ: ____________________ የተሽከርካሪው አይነት______________________________

የጭነቱ አይነትና መጠን:---------------------------------------------

ተሽከርካሪው ይሄድ የነበረው ከ -------------- ወ□ --------------

• የተሽከርካሪው ባለቤት

ስም : ----------------------------------------- አድራሻ------------------- ክልል ----------

ክ/ከ--------------------------------- ወረዳ ------------------------

• ተሽከርካሪውን ይነዳ የነበረው ሰው

ስም : ---------------------------------------- አድራሻ----- ክልል ------------------------

ክ/ከ--------------------------------------------- ወረዳ --------------------------------

•ተሽከርካሪው የሦስተኛ ወገን መድን ዋስትና ነበረው ነበረው ወይ?

አዎ ☐ የለውም ☐ አላወኩም ☐

•ዋስትና ካለው ዋስትናውን የሰጠው ኩባንያ

ስም ------------------------------------------ ቅርንጫፍ ------------------------------------------

የዋስትናው ዘመን: – ከ -------------------- እስከ ---------------------

• አደጋው ከሌላ ተሽከርካሪ ጋር ግጭት ከሆነ

□ሌላኛው ተሽከርካሪ

•□ሠሌ□ ቁዓ ር ---------------------- አይነት : -------------------- የጭነቱ አይነትና መጠን ---------

ባለቤት ስምና አድራሻ ------------------------------ ክልል -------------- ክ/ተ --------- ወረዳ ---------

□ሹ□ሩ ስምና አድራሻ --------------------------- ክልል --------------- ክ/ተ---------- ወረዳ ---------

5.2ተሽከርካሪው ካል□ወቀ

- □ል ታወቀበት ምክንያት :--------------------------------------------------------------------

- □ለው፡ □ቋሚ መረጃ : -----------------------------------------------------------------------

6. አደጋው ሲደርስ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ስምና አድራሻቸው

1. -------------------------------- ክልል ----------- ክ/ከ----------------- ወረዳ --------------

2. --------------------------------- ክልል ------------ ክ/ከ ------------- ወረዳ --------------

**3. ---------------------------------** ክልል ------------- ክ/ከ ----------- ወረዳ -------------

## የካሣ ክፍያ አፈፃፀም ሪፓርት ቅጽ 5

የሚጃ ዓይነት :- በሶስተኛው ወገን ላይ በደረሰው የተሽከርካሪ አደጋ ለሜድን ሰጪዎችና ለሜድን ፈንድ ጽ/ቤት የቀረበው የህክምናና የካሳ ጥያቄ አፈፃፀም ሪፖርት

የሚጃ አዘጋጅ/አቅራቢ፡- በሜድን ሰጪ ኩባንያዎች የሚዘጋጅ በሜድን ኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬት የካሳ ክፍያ ቡድን የሚቀነባበር

የሚጃ ተጠቃሚ :- ጽ/ቤቱና የሜድን ፈንድ ቦርድ

የሚጃው ጥቅም :- ✓ የሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች የካሳና የህክምና ጥያቄ አፈፃፀም ለማላካት፣

✓በያንዳንዱ የሜድን ሰጪ ኩባንያ የሦስተኛ ወገን የካሳ አፈፃፀም ለማ ምገም

✓የተከፈሉና ያልተከፈሉ የካሳ ጥያቄዎችን ለማውቅና ለሚከታተል፣

✓የካሳ ጥያቄ ቀርቦ በምን ግዜ ወስጥ የካሳ ሂደት እደሚፈፀም ለማወቅ፣

✓ለአርቦንና ታሪፍ ማስተካከያ ጥናት ሚጃዎችን ለማሟቸት፣

ሚጃው የሚዘጋጅበት ጊዜ፡- በሦስት ወር አንዴ ሆኖ ከፈንድ አሰባሰብ ሪፖርት ጋር አንድ ላይ፤

## የካሳ ጥያቄ ማጠየቂያ ቅጽ 6

**የመረጃው ዓይነት** ፡- የአመልካቾችና የጥያቄዎቻቸው አጠቃላይ መረጃ ዋና ማዝገባ

**የመረጃው አቅራቢ** ፡-በዳይሬክቶሬቱ የካሳ ክፍያ ባለሙያ ካመልካቾች በሚገኝ መረጃ የሚሞላ

**የመረጃ ተጠቃሚ** – ለ ዳይሬክቶሬቱና ጽ/ቤቱ

**የመረጃው ጥቅም** – የአመልካቾችን ዋና ዋና መረጃ በመያዝ ምንና መቼ እንደጠየቁ ለማወቅ፣

✓የአፈፃፀም ክትትል ለማድረግ፣

✓ለያንዳንዱ አመልካች ፋይል ቁጥር ተሰጥቶ የሚከፈትበት፣

መረጃው የሚዘጋጅበት ጊዜ፡ - የመድን ሽፋን በሌለው ወይም ባልታወቀ ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ፣

## የፈንድ ገቢ ማሰባሰቢያ ቅጽ 7

**የሪፖርቱ አይነት፡ -** የመድን ሰጭ ከባንያዎች የሦስተኛ ወገን የመድን ዋስትና የሸጠላቸው የተሸከርካሪዎች አይነትና ብዛት የሰበሰቡትና ገቢ የአደረጉት የታሪፍ ማጠን ማስታወቂያ

**የሚጃው አቅራቢ** ፡ -የመድን ሰጪ ከባንያዎች

**የሚጃው ተጠቃሚ -** የኦፐሬሽን ዳይሬክቶሬት፤የመድን ፈንድ ጽ/ቤት

**የሚጃው ጥቅም** ፡ - ✓ተጠንቶ ሥራ ላይ የዋለው ታሪፍ በአግባቡ መተግበሩን ለሚጋገጥ

✓ የታሪፍ ማጠን በተሸከርካሪ አይነት ለማወቅ

✓ለአርቦንና ታሪፍ ጥናት ሚጃዎችን ለማሟቸት

**ሚጃው የሚዘጋጅበት ጊዜ፡ -** በየሦስት ወር አንዴ

## የተሸከርካሪ አደጋ ማስታወቂያ ቅጽ 8

**የሪፖርቱ አይነት** :-የሦስተኛ ወገን የመድን ሽፋን በሌለው ወይም ተለይቶ ባልታወቀ ተሸከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ አደጋ መድረሱን ለመድን ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረጊያ

**የመረጃው አዘጋጅ** :- ተጎጂው ወይም የተጎጂው ቤተሰብ ወይም ማንኛውም ሌላ ሰው

**የመረጃው ተጠቃሚ** – የኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬትና ጽ/ቤቱ፣

**የመረጃው ጥቅም** :-✓ስለተጎጂዎች የመጀመሪያ መረጃ ለማግኘትና ዕርዳታ የሚጥበት ሁኔታ ለማመቻቸት፣

✓አደጋ ስላደረሰው ተሸከርካሪ፤ የተሸከርካሪ ባለቤትና የአሽከርካሪወን መረጃ ለማግኘት፣

✓ስለ አደጋው መረጃ ለማግኘትና ክትትል ለማድረግ፣

**መረጃው የሚዘጋጅበት ጊዜ፡** – የመድን ሽፋን በሌለው ወይም ባልታወቀ ተሸከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ፣

## የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ሪፖርት ቅጽ 9

የሚጃው አይነት :-የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት መግለጫ ሐሳብ ማጠየቂያ ቅጽ

የሚጃው አቅራቢ ፡-የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት የሰጠ የጤና ተቋም ወስጥ አገልግሎት የሰጠው የሕክምና ባለሙያ

የሚጃው ተጠቃሚ፡-የመድን ፈንድ ጽ/ቤትና አገልግሎት ሰጭው የጤና ተቋም

የሚጃው ጥቅም ፡-✓የአገልግሎት ክፍያ ለሚፈፀም

✓የጉዳቱ አይነት ማጠንና የተደረገው የሕክምና ዕርዳታ ለማወቅ

✓የሚያስፈልገወን ተከተተይ ሕክምና ለማወቅ

✓የተጠቀሰው የጉዳትና የተሽከርካሪን አደጋ ለማፃፀር

ሚጃው የሚዘጋጅበት ጊዜ ፡-የሕክምና ዕርዳታ በተሰጠ በ10 ቀን ወስጥ